# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፦ ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ግንቦት 7 ቀን 2002 ዓ.ም**

**የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ብጥብጥ ያስነሳው ወያኔ መሆኑ ተጋለጠ፤**

**ከግቢው ወጥተው ወደቤተሰቦቻቸው የሄዱ ተማሪዎች ብዙ በመሆናቸው**

**እስከ ዛሬ ትምህርት አልተጀመረም፤**

**የወያኔ ፍርሀት ምንጭ ምን እንደሆነ ባልታወቀበት በዚህ ወቅት አዳዲስ ድራማ እየፈጠረ በዜጎች ህይወት እየቀለደ መሆኑ ታወቀ፤**

**በአዳባ ከተማ ከ20 ሰው በላይ ሞቱ ከ50 በላይ ደግሞ ክፉኛ ቆሰሉ፤**

**የድርጊቱ ፈጻሚ ወያኔ መሆኑ ተረጋገጠ፤**

**የእምነት አባቶች ከተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ጋር ሊያደርጉት የነበረው ውይይት ሳይሳካ ቀረ፤**

የወያኔው ዘረኛ ቡድን ከበረሀ ጀምሮ ይዞት የመጣውን የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲውን አሁንም እየገፋበት መሆኑን ከሰሞኑ ድርጊት ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በቅርቡ የወያኔ መሰሪ ባህሪ ያልገባቸው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መሀከል የእርስ በርስ ብጥብጥ ተከስቶ ለአንድ ተማሪ ሞት እና ለብዙዎች ጉዳት መዳረግ ምክንያት መሆኑም ታውቆዋል፡፡

በዩኒቨርስቲ ውስጥ ለብዙ ዓመታት ተማሪዎች በአንድነት መንግስታቱን ሲፋለሙና ሲያወግዙ የነበረ ቢሆንም ወያኔ ግን በዘረጋው ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲው አማካኝነት ተማሪዎችን እርስ በርስ እያጋጨ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ቅዳሜ ምሽት ላይ በተጀመረው ብጥብጥ በርካታ ተማሪዎች ተደብድበው ለጉዳት የተዳረጉ ሲሆን አንዱ ተማሪ ስስ ብልት አካሉ ላይ በመመታቱ የተነሳ ህይወቱ ሊያልፍ የቻለ ሲሆን በዚህ ግጭት ውስጥ የተሳተፉት የኦሮሚያ እና የትግራይ ክልል ተወላጅ ተማሪዎች ላይም ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰባቸው ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

የጥፋት እሳት እየለኮሰ በላዩ ላይ ቤንዚን እያርከፈከፈ የሚገኘው የወያኔ ቡድን ተማሪዎችን በዘር ሀረጋቸው ከፋፍሎ እንዲጋጩ ከማድረጉም በላይ አንዴ ለአንደኛው ሌላ ጊዜ ለሌላኛው በመወገን እርስ በርስ እንዲተላለቁ እያደረገ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

በተለይ ቅዳሜ ምሽት ላይ በአዲስ አበባ ስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ ያሉት ተማሪዎች እንደ ወትሮዋቸው በመማር ላይ ውለው ገሚሱ እረፍት ሌላው ደግሞ ቤተ መፃህፍት ቤት ገብተው በማንበብ ላይ እንዳሉ ሁለት የትግራይና የኦሮሚያ ብሔር ተወላጅ ተማሪዎች ሆን ብለው በሞባይል ቀፎ ጠፋ በሚል ሰበብ እንዲጋጩና እርስ በርስ ጠብ እንዲያነሱ ተልዕኮ ከወያኔ ተሰጥቶዋቸው የገቡ በመሆኑ በቀላሉ አንደኛው አጥቂ ሌላኛው ተጠቂ ሆነው ፀብ መጀመሩን የገለፁት የግቢው ተማሪዎች ጉዳዩ እና ዓላማው ያልገባቸው የዋህ ተማሪዎች በፀቡ ውስጥ ተነክረው ግጭቱ እንዲባባስ እና አንድ ተማሪ ምንም በማያውቀው ጉዳይ ሊሞት እንደቻለም በዝርዝር አስረድተዋል፡፡

አስቀድሞ የትግራይ ተወላጆች ናቸው በተባሉ ተማሪዎች ላይ ጥቃት እንዲደርስ ሆን ብሎ ያስጀመረው የወያኔ ደህንነት እና መረጃ መምሪያ የግቢው ተማሪዎች በፀቡ ላይ እንዲረባረቡ ለማድረግ ያሰበ ቢሆንም ግጭቱ ግን ጥቂት የኦሮሞ እና የትግራይ ተወላጅ ተማሪዎችን ብቻ ያሳተፈ ሲሆን ጉዳዩ በአጭሩ ተቀጭቶ ሊቀር የነበረውን ወያኔ መልሶ ሲቪል የለበሱ የደህንነት ሰዎችን ማክሰኞ ሌሊት ወደ ግቢው አስርጎ አስገብቶ አዲስ ብጥብጥ እንዲነሳ ያደረገ መሆኑን የጠቀሱት የግቢው ተማሪዎች በዚሁ ዕለት ብዙ ቁጥር ያላቸው የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ተማሪዎች ጉዳት እንዲደርስባቸው መደረጉንም ተማሪዎቹ ገልፀዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ምርጫ ሊደረግ ጥቂት ቀናት በቀረው ጊዜ ውስጥ ባደረበት ውስጣዊ እና ውጫዊ ፍርሀት ተማሪውን ለሁለት ጎራ ከፍሎ ድጋፍ ለማግኘት ሲል በተማሪዎች መሀከል

ብጥብጥ እና ሁከት እንዲነሳ ያደረገ መሆኑን የጠቆሙት የስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ወያኔ ርካሽ እና ተልካሻ በሆነ ምክንያት ተማሪውን ለመያዝ ያደረገው ሙከራ ሊከሽፍበት እና ድጋፍም ሊያጣበት እንደቻለ ታውቆዋል ብለዋል።

የወያኔ ቡድን የህዝብ ድጋፍ እንደሌለው በመረዳቱ ተማሪውን በግዴታ የአባልነት ፎርም እያስሞላ አባል ቢያደርግም በግዴታ የተሞላ ፎርም ውጤት የማያመጣ መሆኑን ዘግይቶ በመረዳቱ ተማሪውን እርስ በርስ እያጋጨ በመሀከል አንደኛው ወገን እንዲደግፌው ለማድረግ አስቦ የሰራው ቀመር ነው ያሉት እነኚሁ የግቢው ተማሪዎች ወያኔ እንዳሰበው ድጋፍ ሳይሆን ተቃውሞ....... ፍቅር ሳይሆን ጥላቻ...... ማትረፉን በዚያው ዕለት ሊያረጋግጥ ችሎዋል ብለዋል።

ቅዳሜ ዕለት የተጀመረው የተማሪዎቹ የእርስ በርስ ብጥብጥ በደህንነቶች እርዳታና ድጋፍ ማክሰኞ እንደገና ተቀጣጥሎ ዩኒቨርስቲው ለ8 ቀናት ባዶ ሆኖ ሰንብቶ ትምህርት የተጀመረ ቢሆንም አሁንም በተማሪዎቹ ዘንድ ፍርሀት የነገሰ በመሆኑ የረባ ትምህርት መስጠት አለመጀመሩን ተማሪዎቹ አስረድተዋል።

ወትሮም የተማሪዎች ግጭት ሲነሳ ሰርግና ምላሹ የሆነው የፌዴራል ፖሊስ ቅዳሜ ዕለት ፀቡ ከተከሰተበት ዕለት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መትረየስ በተጠመዱ መኪኖች በውጭ ዙሪያውን አጥሮ የሚገኝ ሲሆን በግጭቱ ዕለትም ብዙ ተማሪዎች ጉዳት የደረሰባቸውና አንዱም ተማሪ ሊሞት የቻለው በእነሱ ድብደባ መሆኑን ተማሪዎቹ አጋልጠዋል።

ማክሰኞ ዕለት የደህንነት አባሎች እና የፌዴራል ፖሊሶች በወሰዱት ጨካኝ እና ዘግናኝ እርምጃ ቁጥራቸው የበዛ ተማሪዎች ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ከመሆኑም በላይ አፋጣኝ የህክምና እርዳታ እንዳያገኙ አቅራቢያቸው ወደሚገኙት ሆስፒታሎች እንዳይሄዱ ከልክሎዋቸው ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ለመሄድ እንደተገደዱም እነዚሁ የጉዳቱ ሰለባ ተማሪዎች ሲናገሩ ተደምጠዋል።

ግጭቱ ከተከሰተበት ማግስት ጀምሮ በወያኔ ድርጊት የተበሳጩ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ተማሪዎች ወደ የቤተሰቦቻቸው የተጉዋዙ ሲሆን ተማሪዎቹ በየሄዱበት ቦታ የማጥላላት ዘመቻ ሊሰሩብኝ ይችላሉ በሚል ስጋት እና ፍርሀት ትምህርታቸውን እንዲጀምሩ የማስጠንቀቂያ ማስታወቂያ ያወጣ ቢሆንም እስከ አርብ ዕለት ድረስ ተማሪዎቹ ወደ ትምህርት ገበታቸው አለመመለሳቸውን ከተማሪዎቹ ገለፃ ለመረዳት ተችሎዋል።

በአሁኑ ሰዓት ምርጫው ሊደረግ ጥቂት ቀናት በቀረበት ወቅት ወያኔ የተለያዩ ወንጀሎችን እየለጠፈ ድራማ በመስራት ላይ የሚገኝ በመሆኑ መላው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የዚህ ድራማ ሰለባ እንዳንሆን ልንጠነቀቅ ይገባል ሲሉም ተማሪዎቹ ምክር አዘል ሀሳብ ሰንዝረዋል።

ከትላንት በስቲያ የወያኔ ስርዓት ቁንጮ የሆነው በረከት ስምኦን ለጋዜጠኞች በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መሀከል የተከሰተው የግጭቱ መንስኤ የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ (ኦህኮ) የተባለው በዶክተር መረራ ጉዲና የሚመራው እና አረና የተባለው በገብሩ አስራት

የሚመራው ፓርቲ ሁለቱ የፈጠሩት ችግር ነው ሲል መግለጫ የሰጠ ሲሆን ዶክተር መረራ በበኩላቸው ዙሪያው ገደል ሲሆንባቸው እና ማጣፊያው ሲያጥራቸው የሰጡት ምክንያት ነው ሲሉ ማጣጣላቸው ታውቆዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔው ቡድን ባደረበት ፍርሀት የተነሳ በተናጠል እና በቡድን ስም እየጠራ ማብጠልጠል ከመጀመሩም በላይ እያስፈራራ የምርጫው ሁኔታ አቅጣጫው እንዲቀየር ከፍተኛ ግፊት እያደረገ መሆኑ ተነገረ::

::

የግድያና የማዋከብ ዘመቻው ቀጥሎ ባለበት በዚሁ ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ ዶክተር መረራ ለቅስቀሳ በምዕራብ ሸዋ ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ባሉበት ወቅት የሚያሽከረክሩዋት መኪና በአምቦ ከተማ ባደሩበት ሆቴል ውስጥ መስታወቱ ተሰባብሮ ብዙ የምርጫ ነክ ሰነዶች ከመወሰዱም በተጨማሪ አራቱም ጎማዎች ተፈትተው የተወሰደ መሆኑን ከአምቦ የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

ወያኔ በሚፈጽማቸው ግፍና መከራ ብሎም ማዋከቦች እጅግ ግራ የተጋቡት የሀገሪቱ ህዝቦች ከወዲሁ በምርጫው አስጊ ሁኔታዎች እየታዩ በመሆኑ ሊፈጠር የሚችለው ሰብአዊ ቀውስ ከባድ ሊሆን ይችላል በሚል በአንክሮ እየተከታተሉ ይገኛሉ::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ በአርሲ አዳባ ከተማ የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት ኦህዴድ የተመሰረተበትን 20ኛ ዓመት በዓል በማስመልከት በከተማዋ መሰብሰቢያ ሜዳ ላይ በግዳጅ እንዲወጣ በተደረገው ህዝብ መሀከል የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ሰራተኞች የእጅ ቦምብ ጥለው ከ20 በላይ ሰዎች እንዲሞቱና ከ50 በላይ የሆኑት ደግሞ ክፉኛ እንዲቆስሉ የተደረገው የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማስፈራራት እና ለማጥላላት ሲሆን ህዝቡ መሀከልም ፍርሀት እንዲፈጠር ለማድረግ ሆን ተብሎ የተሰራ መሆኑን ከአርሲ የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል::

የወያኔው ቡድን የፍርሀቱ ምንጭ ምን እንደሆነ በውል ባልለየበት በአሁኑ ወቅት የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ ሲሆን ሐሙስ ዕለት ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም ደግሞ ሌላ አዲስ መመሪያ ማውጣቱ ታውቆዋል::

ይህ አዲስ የወጣው የወያኔ መመሪያ ምርጫው እስኪጠናቀቅ ድረስ ማንኛውም ተቀማጭነቱ ኢትዮጵያ የሆነ አምባሳደር ወይም ዲፕሎማት ከአዲስ አበባ ውጭ መውጣት እንደማይችል የደነገገ ሲሆን ለመውጣት ቢፈልግ እንኳዋን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከምርጫ ጋር የማይገናኝ የይለፍ ደብዳቤ እንደሚሰጥ በይፋ አውጆዋል::

የግብረ ሰናይ ድርጅት መሪዎች እና ሰራተኞችም ከግንቦት 13 ቀን እስከ ግንቦት 17 ቀን ድረስ ከአዲስ አበባ ውጭ መንቀሳቀስ የተከለከሉ መሆኑን የደነገገው የወያኔ ቡድን በምርጫ እንደሚሸነፍ ከወዲሁ ስላወቀ ለማጭበርበርና ኮሮጆ ለመገልበጥ እንዲችል ብቻውን ያለማንም ታዛቢ ለመፈፀም እንዲረዳው ነው ሲሉ ዲፕሎማቶቹ ሲገልጹ ማድመጣቸውን ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል።

በተደጋጋሚ ጊዜ የምርጫውን ሂደት እንታዘብ ብለው ጥያቄ ሲያቀርቡ የቆዩት ዲፕሎማቶቹ እስከ ዛሬ ድረስ ምላሽ ሳይሰጣቸው ቆይቶ ከትናንት በስቲያ ግን በመግለጫ እንደማይፈቀድላቸው ይፋ አድርጎዋል።

ዜጎች በየሜዳው ላይ በወያኔ ቅልብ ጦር እንደ ቅጠል ሲረፈረፉ ትንፍሽ ያላሉት የእምነት አባቶች በበኩላቸው ሰሞኑን ለተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች እና አባሎቻቸው የማደናገሪያና የማስመሰያ ጥሪ ማድረጋቸው ታውቆዋል።

ወያኔ በላካቸው እና በነገራቸው መሰረት እራሳቸው እንዳሰቡና እንደፈለጉ አስመስለው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን ለማነጋገር እንፈልጋለን ብለው ደብዳቤ የበተኑ ቢሆንም አብዛኛው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች እንደማይገኙና እንደማይካፈሉ ከመግለፃቸውም በተጨማሪ እስከ ዛሬ ድረስ በሀገሪቱ ዜጎች እንደ በሬ እየታረዱ እያዩ ምንም ያልተናገሩት የእምነት አባት ነን ባዮቹ........ ያለ ሀጢያትዋ የታሰረችው ብርቱካን ሚደቅሳን ሳያስፈቱ.......ወያኔ በህዝብ ላይ ግፍና መከራ እየሰራ እያዩና ተባባሪ ሆነው እያለ........ ህዝብ እንዳይጎዳ ብለው ለይምሰል እናነጋግራችሁ ማለታቸው ቀልድ እና ፌዝ ነው ሲሉም ተሳልቀውባቸዋል።

ለምርጫው ቅስቀሳ ይረዳ ዘንድ ገንዘብ እና መኪኖችን የለገሱት አባ ጳወሎስ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ነፍስ አባት መሆናቸው እየታወቀ እንዴት ገለልተኛ ሆነው ሊያነጋግሩ ይችላሉ ብለው የሚጠይቁት ተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎቹ በህዝብ ላይ በየእለቱ የሚከመረውን የኑሮ ውድነት እንዴት ይቃለልለት ብለው አንድም ቀን ሳይጨነቁ ዛሬ ደርሶ የእምነት አባት መስለው መታየታቸው የወያኔን ተልዕኮ ለማስፈፀም ብቻ መሆኑን አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል።

በ1997 ዓ.ም በተከሰተው የህዝብ እልቂት ወቅት በየዋሻቸው ተደብቀው የነበሩት የእምነት አባቶች ነን የሚሉቱ ህዝቡን እንዲያድኑ ተደጋጋሚ ጥሪ ቢቀርብላቸውም የመለስን ቁጣ ፈርተው ዝም እንዳላሉ ወያኔ ዛሬ በህዝብ ዘንድ ተቃውሞ እና ጥላቻ ሲሰነዘርበት በአሳቻ መንገድ ገብተው የህዝቡን ሀሳብ ለማስቀየር ደፋ ቀና ማለታቸው እጅግ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያሳፍር ነው ሲሉም በቁጭት የሚገልፁ ወገኖች በርካቶች ናቸው።

ግራ የተጋባው የወያኔ አረመኔ ቡድን አንዱን ከቦሌ ......ሌላውን ከጉለሌ....... እንዲያም ሲል ከሰላሌ ..........እያነካካ የገዛ አባሎቹን ጭምር እያመሰ በመሆኑ የምክር ቤት አባሎች ናቸው የተባሉት ሁሉ ተቃውሞና ስድብ እየሰነዘሩበት ይገኛሉ።

ለመውለድ ቀኑዋ እንደ ደረሰ ሴት እየተቁነጠነጠ የሚገኘው ዘረኛው እና አምባገነኑ የወያኔ ቡድን እንደ ሽንኩራ አገዳ መጥጦ መጣል ልማዱ በመሆኑ አምና ለምክር ቤት አባልነት መርጦ

ያመጣቸውን ዘንድሮ ሙሉ ለሙሉ በዕጩነት ሳያቀርባቸው በመቅረቱ በመበሳጨታቸው አድማ ማድረጋቸው ተረጋግጦዋል፡፡

ከገጠር ፊደል መቁጠር የማይችሉ መሀይማን ሰብስቦ እጅ አውጡ ሲሉዋቸው የሚሰቅሉ አውርዱ ሲሉዋቸው የሚያንጠለጥሉ ተንቀሳቃሽ ሮቦቶችን አግበስብሶ የነበረ ሲሆን ዘንድሮ ከ90 በመቶ በላይ የሆኑትን እነዚሁ የምክር ቤት አባሎች ምርጫ ውስጥ እንዳይሳተፉ አድርጎ አውላላ ሜዳ ላይ በመጣሉ በብስጭት ተደጋጋሚ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ አንገባም በማለት አድማ ማድረጋቸውን ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ዙሪያው ገደል የሆነበት የወያኔ ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ግብግብ በገባበት በአሁኑ ወቅት.......ከራሱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ኩርፊያ ባየለበት......ዲፕሎማቶች የስንግ ይዘው አላላውስ ባሉበት በዚህ አጣብቂኝ ወቅት የፓርላማ አባሎች እንደገና በችግሩ ላይ ተጨማሪ ችግር መሆናቸው እጅግ እንዳንገበገበው የገለፁት የፓርላማ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ለአንዱ ቀን አድማ መደረግ ሲገርመው ሁለተኛውንም መድገማቸው ተስፋ እንዳስቆረጠው ገልፀዋል፡፡

የምክር ቤት ስብሰባዎቹ በሳምንት ሁለት ጊዜ ማክሰኞ እና ሐሙስ ዕለት የሚደረጉ ቢሆንም ሁለቱንም ቀናት ሰርዘው በራሳቸው ጊዜ በመቅረታቸው የተበሳጨው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ አባሎቹ በአስቸኳዋይ እንዲሰበሰቡ አጭር እና ጥብቅ ትዕዛዝ ለአፈ ጉባዔው ተሾመ ቶጋ ትእዛዙ ተግባራዊ መሆን ያለቻለ መሆኑ ታውቆአል፡፡

ለምን ምርጫ ውስጥ አልገባንም ብለው አኩርፈው አድማ ያደረጉት የወያኔ ፓርላማ አባሎች ከሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም በሁዋላ ጉዋዛቸውን ጠቅልለው ወደ መጡበት እንደሚመለሱ በማስታወቂያ ሰሌዳቸው ላይ የተለጠፈው ፕሮግራም ያስረዳል፡፡